# ★ዴሞክራሲያ★

* የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ ፓርቲ ልሳን *

ዴሞክራሲያ ቅጽ 33 ቀቁር 7 ሚያዚያ 2000 ዓ.ም.


## ኢሕአፓ 36 ዓመት - ትግል ሲዘከር፣ ቃል ኪዳን ሲታደስ

ፍኖተ ገድል ድምፁ ከሩቁም ባልተሰማበት፣ ፍኖተ ድል ኪል ኪል ሊል ቀርቶ የህልም ቃጭል በነበረበት፣ አመፅን ማደራጀት ቀርቶ ማሰቡ ወንጀል አሊያም ቅዠት ተብሎ በተፈረጀበት፣ ገዢዎች በሥልጣን የሚቀመጡት በአምላክ ፍቃድ ነው ተብሎ በሚለፈፍበት፣ ግራ ቀኙ ላይ ታቹ ጨልሞ በነበረበት፣ ይቻላል ተራ ቃል ሳይሆን አደገኛና ለቅጣትም የሚዳርግ ሆኖ በተገኘበት፣ ማለትም አብዮትን ማሰቡ ያኔ አንዳንዶች ይሉት እንደነበረው ከብዙ ትውልድ በኋላ መነሳት ያለበት ጉዳይ ነው ይባል በነበረበት፣ ባጠቃላይም የሕዝብ ሉዓላዊነት ላይ እምነት ባልነበረበት፣ የነገንና የተነገ ወዲያን ብሩህ ኮከብ ከወዲሁ በተስፋ በማየት ሰፍኖ የነበረውን ሥነርዓት ማቸነፍ ይቻላል ብለው፣ ጨለማውን ለማስወገድ ክብሪት የጫሩ፣ ብርሃን የፈነጠቁ በኢትዮጵያ የትግል ታሪክ የክብር ቦታቸውን የሰጡ የኢሕአፓ አባላት ምን ጊዜም ህያው ሆነው የሚኖሩ በዚሁ በግንባር ቀደምነት ለተደረገው የትግል አስተዋፅዖ ምን ጊዜም የሚመሰገኑ ናቸው::

የድርጅት ዕድሜ በደፈናው ዓመት አልፎ ዓመት ሲተካ የሚደረግ ትረካ ሳይሆን የታሪክ ጎማ በመንገዱ ያገኘውን እየጨፈለቀ ሲሄድ ህልውናን ጠብቆ፣ መከራና ስቃዩን ተቋቁሞ፣ ቃል ኪዳኑን ሳይከዳ ፀንቶ መቆሙንም አመልካች ነው:: ስንቱ ድርጅት አለሁ አለሁ ብሎ እንደ ጤዛ ከመቅፅበት ሲጠፋ ደግሞ፣ የቆየውና የበረከተውን ማድነቁ ወይም በበጎ ማየቱ ሲያንስ ነው:: ከ36 ዓመት በፊት ኢሕአፓን የመሰረቱት ዛሬ መስዋዕትን ከፍለው አብዛኞቹ በሕይወት ባይኖሩም በፊውዳል ጨለማ የሕዝባዊ ሥርዓት ኮከብን ማየት የቻሉና አይቻልም የሚለው አመለካከት ሰፍኖ በነበረበት ወቅትም ለውጥም አብዮትም ይቻላል ብለው የደፈሩ ታሪክ የማይረሳቸው ጀግኖች ነበሩ:: ለሰባት ቀን የተካሄደው መሥራች ጉባዔ በኢትዮጵያ የያኔው ተጨባጭ ሁኔታ ላይ ሰፊ ውይይትን አድርጎና መደረግ በነበረበት የትጥቅ ትግል ላይ ተገቢውን ውሳኔ ያሳለፈ ከመሆኑም በላይ በዚሁም ረገድ ዝግጅቱ ተጀምሮ የሠራዊት ምሥረታው ሂደት እውን የሚሆንበት ሁኔታ ተመቻችቷል:: ኢሕአፓ በተመሰረተበት ጊዜ የአፄው ሥርዓት የማይደፈር የማይገረሰስ እንዲሁም ኃያል ተብሎ የሚታመንና

በአሜሪካም ድጋፍ ተጠናክሮ የነበረ በመሆኑ፣ ማን ሊነቀንቀው ይችላል ተብሎ እየተነገረና የተማረውም እንቅስቃሴ በየጊዜው እየተመታ የነበረበት ወቅትም በመሆኑ፣ ልፈነዳ ነው ይል የነበረውን እሳተ ጎመራ የሚያዳምጥ ጆሮ የጠፋበት ወይ ያነሰበት ጊዜ ነበር፡፡ በሕዝብ ባለድልነት ላይ ፅኑ እምነት የነበራቸው የኢሕአፓ መሥራቾች ግን ከደይኑ ባሻገር ብርሃንን፣ ጨለማ ቢሰፍንም ጎህን አይተው፣ ተገዢ በተባለው ሕዝብ ላይ እምነትን አሳድረው፥ ለኢትዮጵያና ለሕዝባችን እንታገላለን ብለው ሲነሱ የባዕድ እርዳታ ወይም ድጋፍ አለን የለን በሚል ሳይጨነቁ ሙሉ እምነታቸውን በሕዝብ ላይ አድርገው ነበር፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝብም አላሳፈራቸውም--የካቲት አብዮትን አምጦ ወልዶ ታሪካዊ ለውጥን አመጣ፡፡ ኢሕአፓም ለዚህ ለወጥ የበኩሉን አስተዋፅዖ ቢያደርግም አቅሙ ገና ለጋ በመሆኑ የአብዮቱን ፍሬ የታጠቁ መኮንኖች ከሕዝብ ላይ ሲቀሙ ሊያግዳቸው አልቻለም፡፡ ቀማኞዎቹ ግን የማይደላደሉበትን ሁኔታ ለመፍጠር አልተሳነውም - ታግሎና የደም ግብር ከፍሎ፡፡ 36 ዓመታት የከባድ ትግል ዓመታት መሆናቸው ኢሕአፓን አልፈታውም፡፡ በየቀበሌው ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግስት ይመሥረት፣ ዴሞክራሲ አለገደብ ለጭቁኖች፣ መሬት ለአራሹ እያሉ ለጋ ሕይወታቸውን ለሕዝብ የሰጡትን ስናስታውስ ታሪክ አበላሾች ዛሬ ወጣቱ አለቀ እንደሚሉት ሳይሆን ወጣቱ ለሀገሩ በጀግንነት እየተሰዋ፣ ታሪክን እየፃፈና ባንዳን እያሳፈረ በመታገሉ፣ ኢሕአፓ ለቅርስ የሚሆን ሚናን ተጫውቷል፡፡ የሀገሪቷ እንባና ሰቆቃ ያነሳሳው የኢሕአፓ ትውልድ የተጨባጭ ትግል ተመክሮው ውሱን ቢሆንም ቆራጥነትና ጀግንነት ያነሰው ባለመሆኑ በትግሉ እየተማረ፣ ደሙን አፍሶ፥ ንቃቱን እያሳደገ ሁሌም ለኢትዮጵያ ቆሞ ትግሉን ሊያስፋፋ ችሏል፡፡ ለውሱን ድርጅታዊ ጥቅም በሚል ግን የሀገሪቷን ዘላቂ ጥቅም አሳልፎ ለመስጠት ዝግጁ ባለመሆኑም የደረሰበት ጉዳት በቀላሉ የሚገመት አይደለም፡፡ ኢሕአፓ ለባዕድ ሀገሮች - ለቅርቡም ለሩቁም፣ ለኃይለኛውም ደከም ላለውም -፣ ለአካባቢ ግንባሮች…ወዘተ መጎንበሱን አሻፈረኝ በማለቱ፣ የኢትዮጵያን ጥቅም አሳልፎ ለመስጠት ባለመስማማቱ ጠባቦችም ባዕዳንም አብረው ተነስተውበት ብዙ ጉዳትን መቀበል ተገዷል፡፡ ሥርዓተ አልበኛ፥ የሲ.አይ.ኤ. ቅጥረኛ፥ አባይ ኢትዮጵያ፥ ትምክህተኛ፥ አስገንጣይ፥ ቅጥረኛ ነፍሰ ገዳይ፥ ወዘተ… ወዘተ…፥ ያልተባለውና ያልተጫነበት ፀያፍ ቅፅል አልነበረም፡፡ ድርጅቱ በሰላም ሊታገል ዝግጁ ሆኖ ሳለ፥ የፖለቲካ ትግሉን እያካሄደ ሳለ፥ ጦርነት አውጅውበት ሳለ፥ ጅራፍ እራሱ ገርፎ እራሱ ይጮኻል ዓይነት ጦርነት ከፈተብን በሚል ሽብር ከፈቱበት፡፡ የሕዝብን የእኩልነት መብትና የሀገርን አንድነት በመደገፉ ይህ አልዋጥ ያላቸው ክፍሎች በአንድ ጎኑ ግንጠላን ደገፈ፣ የሶማሊያን ወራሪ ጦር ደገፈ፥ አበረታታ፥…ወዘተ ብለው ሲቀጥፉ በሌላ በኩል ደግሞ ድርጅቱን በትምክህተኛነትና ፀረ-ጭቁን ብሔረሰቦች ትግል አቅዋም ይዟል ብለው የከሰሱትም፣ ተባብረው የወጉትም ነበሩ፡፡ ኢሕአፓ ግን መቸም ቢሆን መች የኢትዮጵያን ጥቅም የሚፃረር አቅዋም እንዳልያዘ ታሪክ ራሱ ምስክር ነው፡፡ ለሚሰነዝሩበት ክሶች ምንም መረጃ በማጣታቸው ከአሉባልታነት ማለፍ ያቃታቸውም በዚሁ ምክንያት ነው፡፡

መሬት ለአራሹ፣ መብት ለጭቁኑ፣ የሀገር ሉዓላዊነት ይጠበቅ፣...ወዘተ በሚሉ መሠረታዊ ዴሞክራሲያዊ መፈክሮች ዙሪያ የተካሄደው ሕዝባዊ ትግል ሰፊ ድጋፍ ያገኘው ጥያቄዎቹ የሕዝብ በመሆናቸው ነው። በፖለቲካው ትግል መድረክ ሕዝብ ለኢሕአፓ ግልፅና የማይካድ ድጋፍ በመስጠቱ ይህን መቋቋም ያቃተው ፋሺስታዊ አገዛዝ ነበልባልና ሌላ አፋኝ ኃይሎቹን አሰማርቶ በነፃ እርምጃና ቀይ ሽብር ኢሕአፓን ሊያጠፋ ተነሳ። አሰቃቂ እርምጃዎችን ወስዶ ብዙ ደምን ካፈሰሰ በኋላ ኢሕአፓ የመከላከል እርምጃን በወሰደ ግድያውን እንደጀመረ አድርገው እያቀረቡ እስካዛሬ ወንጀላቸውን ደብቀው ሚቹን ሲወነጅሉ እየሰማን ነው። በርግጥ ኢሕአፓ በትግል ሲሰማራ ዛሬ ያለውን ተመክሮ የያዘ አልነበረምና በተጨባጭ ትግል ሂደት የፈፀማቸው ስህተቶች እንደነበሩ የሚካድ አይደለም። ድርጅቱ ራሱ ከዓመታት በፊት የሰራቸውን ስህተት ዘርዝሮ ግለ-ሂስ አድርጓል--ግን ትግሉን በማካሄዱ አጠፋሁ አላለም፣ ሊልም አይጠበቅም። ለባዕድ የሀገርን ጥቅም አሳልፎ መቸም ሰጥቶ ስለማያውቅ በዚህም አጠፋሁ የሚለው የለም። ለድርጅታዊ ጥቅም ሲልም ለሀገር የማይበጁ አቅዋሞችን ተቀብሎ ባለመሄዱም በሂደቱ ጉዳት ቢደርስበትም ፀንቶ የቀጠለ በመሆኑ ኩራት እንጂ ንስሀ ዕጣው ሊሆን አይችልም። ኢሕአፓ ለጨለማ ጊዜ ብርሃን፣ ለመከራ ጊዜ ብልት ሆኖ በመባጀቱ ለሰማዕቱና ለደገፉት ሁሉ አኩሪ ታሪክ ነው። ተንከባክበውም የሚይዙት ቅርስ ነው።

በመሆኑም በየጊዜው በድርጅቱ ላይ የተነሱ የውስጥና የውጭ ጥቃቶችን አባላቱና ደጋፊዎቹ በትግል አክሽፈው እነሆ ለ36ኛው የትግል ዓመት አድርሰውታል። የጀመሩ ሁሉ ይጨርሳሉ ማለት አይደለምና፣ ቃላቸውን መልሰው የሚበሉ ጥቂቶች አይደሉምና፣ ትግል ሲመር ይጥመናል ባዮች የነበሩ ቢሆንም በዚሁ ግን ከልብ አማኙ ሁሉም አልነበሩምና ከወታደራዊው አገዛዝ ጋር ትግሉ ሲፋፋም ወገቤን ያሉና ለባለነፍጥ መጎንበስን ባማሩ ቃላት ሸፋፍነው ክህደትን ሊያሰፍኑ የተነሱ ነበሩ- አፍራሽ አንጃዎች። በድርጅቱ ላይ ይህ ነው የማይባል ጉዳት አድርሰው ለአገዛዙ ቢጠቅሙም በዚሁ ፋሺስት ኃይል ከመመታት አላመለጡም። ይህ የከተማው በሽታም በገጠር በሠራዊቱም ብቅ ሊል ሞክሮ በአጭር ሲቀጭ ውሎ አድሮ ግን ብተና በተባለ አጥፊ እንቅስቃሴ መሠረት ብቅ ብሎ ሠራዊቱን ከመበተን አንፃር ከፍተኛ ጉዳት አድርሷል። የብተናው መሪዎች አንዳንዶቹ ራሳቸውን ለቅሌት ስደት ሲዳርጉ ከፊሎቹ ደግሞ ከወያኔ ጋር ለመለጠፍ÷ ለወያኔ ለማደር ሲሄዱ፣ ቆራጥ የኢሕአፓ ታጋዮች ግን መከራውን ችለው ሠራዊቱን እንደገና በእግሩ አቁመዋል። ትግሉም ካለፈው በበለጠ ግለትና ስፋት ሊቀጥል ችሎ ኢሕአፓ ለሀገርና ለሕዝብ የገባውን ቃል ኪዳኑን አክብሮ ተገኝቷል። ለድርጅቱ ቀጣይነት መስዋዕትነት የከፈሉትና የጨለምተኝነትን ጣረሞት ያሸነፉት ኢሕአፓዎች ሁሌም የሚዘከሩና የሚወደሱ ሲሆኑ ይህ ድርጅትን አፍራሽ ተጎንባሽነት አባዜ ለአንዴም ለሁሌም ያልተቸነፈ በመሆኑ በየጊዜው እያገረሸ ድርጅቱን መፈታተኑም አልቀረም። 36 ዓመታት የውስጥም የውጭም ጥቃት የኢሕአፓን ህልውና ሊሰርዝ አልቻለም - አንድ ኢሕአፓ፣ ቋሚ ሕዝባዊ መርህ፣ ፍንክች ንቅንቅ የማይል ኢትዮጵያዊነት!

ኢ.ሕ.አ.ፓ በመሠረታዊ አቅዋሙ ፀንቶ ቢቀጥልም በተቀያየረው ሁኔታ አስፈላጊ የሆኑትን ለውጦችንም አድርጎ፣ መርኃ ግብሩንም አስተካክሎ ታግሏል። ሲመሠረት በነበረው ተጨባጭ ሁኔታና በነበረው የርዕዮተዓለም እምነት መሠረት የወሰዳቸውን አንዳንድ አቅዋሞች መርምሮና በተጨባጭም መንግሥት ነኝ ባዩ ኃይል የወሰዳቸው የማገር እርምጃዎች፣ በኤኮኖሚው ላይ ያደረሰውንም ቀውስ በመታዘብ የቅይጥ ኤኮኖሚና የመድበለ-ፓርቲን ሥርዓት ጠቃሚነት በጊዜ አቅርቧል። በአገዛዞች ስህተትና ትምክህት፣ በተከተሉት የተሳሳተ ፖለቲካ የተነሳ የሀገሪቷ አንድነት ለአደጋ በመጋለጡም ብሔረሰቦችን አፋቅሮ ያስተሳስራል ብሎ ባሰበው መርህ መሠረት ያቀረበውን መፍትሄ በጠባቦች በግልቡ ተወስዶ የመገንጠል አማራጭ በዋናነት በመገፋቱ ኢ.ሕ.አ.ፓ አቅዋሙን በግልፅ በማሰቀመጥ የመገንጠልን አማራጭነት በአሉታዊ አሰቀምጦና ለኤርትራም የፌዴራልን መፍትኄ በማቅረብ ለዚህ አቢይ ችግር ማሳረጊያ ለመስጠት ሞክሮ ነበር። በኢትዮጵያ የነበረውን የብሔረሰቦች ችግር ኢ.ሕ.አ.ፓ የወለደው ሳይሆን አገዛዞቹ ያመጡትና እኩልነትን ከተፃረረ አምባገነናዊ ፖለቲካ የተፈጠረ ነው። ኢ.ሕ.አ.ፓ ሕዝብን አስተባብሮ ሊያታግል ሲነሳ ለዚህ ጥያቄ የበኩሉን ዴሞክራሲያዊ ምላሽ ለመስጠት ሞክሯል። ኢ.ሕ.አ.ፓ ያለፈበት የተማሪውና የተራማጆች እንቅስቃሴ በብሔረሰብ ያልተከፋፈለ ከመሆኑ ሌላ ኢ.ሕ.አ.ፓም በይዘቱና በእምነቱ ሙሉ በሙሉ ኢትዮጵያዊ እንጂ የብሔረሰብ ድርጅት አልነበረም። ብሔረሰብን ቆጥሮ ጠቦና ጎጠኛ ሆኖ የሚገኝ ሁሉ ቦታውና ሰልፉ ከኢ.ሕ.አ.ፓ አልነበረም፣ አይደለምም። ለዚህም ነው ኢ.ሕ.አ.ፓ ጠባቦችን ጊዜ ሳይወስድ የታገላቸው፣ እነሱም ጊዜ ሳይሰጡ ሊወጉትና ሊያጠፉት የጣሩት። የሀገሪቷን ዋና ዋና ችግሮች ለመፍታት ኢ.ሕ.አ.ፓ የነበረውን መንገድ በተግባር እየፈተነና ከሕዝቡም ይበልጥ ሲዋሀድ የተሻለውን መፍትኄ ለመረዳትም እየቻለ የሚስተካከለውን እያስተካከለ ለመታገል ችሏል። ኢ.ሕ.አ.ፓ በሶቭየት ኅብረትና በምስራቅ አውሮጳ፣ አልፎም በቻይናና አልባኒያ ሰፈነ የተባለው ሶሻሊዝም የጥቂቶችን አምባገነናዊ አገዛዝ ሽፋኝ ነው ብሎ አውግዞ ከዚያም በላይ የመድብለ ፓርቲ ሥርዓትን ጠቃሚነት ከነቃሉ ራሱ በይፋ ሲያቀርብ ወያኔ አፋኙን የአልባኒያ ሥርዓት እያዳነቀ፣ ኢ.ሕ.አ.ፓን በአድህሪነት እየከሰሰ፣ ማሌሊትንም መሠረትኩ ብሎ ሲደነፋ እንደነበር ማስታወሱ በቂ ነው። ኢ.ሕ.አ.ፓ ግን ቋሚ መርህና እምነት አድርጎ የያዘውና ዛሬም ሶሻል ዴሞክራሲ ያዋጣናል ሲል የሚያስቀድመው የሰፊውን ሰርቶ አደር ሕዝብ ጥቅም ነው። መረን የለቀቀ ብዝበዛ ሰፍኖ ሰርቶ አደሩ ሕዝብ ለጥቂት ከበርቴዎች ዘመናዊ ባርያ የሚሆንበትን፣ አርሶ አደሩ ለማያባራ ድኽነት የሚዳረግበትን፣ ብዙሀኑ በሀገራቸው የበዪ ተመልካች ሆነው የሚሰቃዩበትን፣ የሀገር ነጋዴና አምራች በባዕዳን የሚጫጫበትን ሥርዓት ኢ.ሕ.አ.ፓ በፊትም አልደገፈም፣ ዛሬም አይደግፍም።

ኢ.ሕ.አ.ፓ መርኃ ግብሩን በተመለከተ ከተቻለና ዴሞክራሲያዊ ሁኔታ ካለ በሰላም ለመታገል መወሰኑን በግልፅ አስፍሮም ነበር። በዚያም መሠረት ምርጥ መኮንኖችን የታገለው በሰላማዊ ሰልፍ፥ በምስጢር በሚበተኑ በራሪዎች፥ ሕዝብን በየፈርጁ በማደራጀትና የተገኘውን መድረክ ሁሉ በመጠቀም ነበር። አገዛዙ ግን በፖለቲካው መድረክ ኢ.ሕ.አ.ፓ እያሸነፈው ስለመጣ በድርጅቱ ላይ

በይፋ ጦርነትን አውጆና አፋኝ ኃይሎቹንም አሰማርቶ የግፍ ግድያውን ተያያዘው:: በየቀበሌው የተረሸኑት፣ በሠራተኞች ቀን የተጨፈጨፉት፣ በአስበ ተፈሪ፥ ጅማ፥...ወዘተ በእነ ጌታቸው ሺበሺና አሊ ሙሳ የተገደሉት ለዚህ ምስክር ናቸው:: አፈናው ሲበዛ ጦርነቱም ሲታወጅ ኢሕአፓ በከተማም በገጠርም የመከላከል እርምጃዎችን መውሰድ ተገዷል:: ለዓመታትም በትጥቅ ትግል የቀጠለውም በጦርነት ፍቅር ሳይሆን ለትግሉ ሌላ አማራጭ በመጥፋቱ ነው:: ወያኔም ለሥልጣን ሲበቃ ኢሕአፓ በሕጋዊና ሰላማዊ መንገድ ለመታገል የነበረውን ፍላጎት ገልጦ ነበር--ዴሞክራሲያዊ መብቶች ከተከበሩ፣ የታገቱት ከተለቀቁም:: ለዚህ የተገኘው ምላሽ ያው የተጠናከረ አፈና ሆኗል:: የታጋይ ኃይሎችን የትግል ስልት የሚወስነው ገዢው ወይም በሥልጣን ላይ ያለው ቡድን ሳይሆን ተጨባጩ ሁኔታ ነውናም የወያኔ አገዛዝ ይዘቱና ጠባዩ ፀረ ሰላም በመሆኑ ይህን ፀረ ኢትዮጵያ ኃይል ከሥልጣን ማስወገድ የሚቻለው በሁለ-ገብ ትግል መሆኑን ኢሕአፓ ከማቅረቡ ሌላ በዚህም በተግባር ለማሰማራት ሞክሮ እንደነበር ይታወሳል:: የትግሉ ስልት በተጨባጭ እውን ሊሆን የሚችልበት ቁሳቁሳዊና የደጀን ሁኔታ ተሟላ አልተሟላ መከተል ያለብንን ስልት ምን መሆን እንዳለበት የሚለውጥ አይደለም:: ኢሕአፓ በልዩ ልዩ የትግል ስልት ሰፊ ተመክሮን ከመገብየቱ ባሻገር ትግሉ ግድ የሚለውን መስዋዕትነትንም በድፍረት ከፈለ እንጂ ከተኩሱ ቀጠናና አውድማ ርቆ ግፋ በርታን አላስለመደም:: በትግሉ መስክ በከተማም በገጠርም የተሰውት በርካታ አባላት ብቻ ሳይሆኑ በጀግንነት የሞት ፅዋን የጠጡት አመራሮቹም ለዚህ ምስክር ናቸው::

ሕዝብ ተባብሮ ቢታገል ፍኖተ ድል ይደመጣል በሚልም ኢሕአፓ ከተመሰረተ ጊዜ ጀምሮ ከሌሎች ድርጅቶች ጋር ለመተባበር ጥረትን አድርጎ በተቻለበትም የኅብረት ግንባሮችን ለመመስረት የአቅሙን አስተዋፅዖ አድርጓል:: የሀገርን ጥቅም በማስቀደምም ትላንት ከገደሉትና ካደሙትም ጋር ሳይቀር ኅብረትን መሥርቷል:: ሁሉንም ሊያስተባብር በሚችል መርኃ ግብር መሠረት ተያይዞ መታገል በሚልም ኢሕአፓ በእኩል ደረጃ ከሌሎች ጋር በመቀናጀት ለመታገል ያደረገውን ጥረት ሁሉም የሚያውቀው ነው:: ድርጅቶች ጠንካራ ደካማ ናቸውና፣ የየራሳቸው ታሪካዊ ሂደት አላቸውና ሁሌም ሀገርን ያስቀደመ ኅብረት የሚለው ፍላጎት እንቅፋትና ደንቃራ በተደጋጋሚ አጋጥሞታል:: ይህ እንዳለ ሆኖ ግን የታጋይ ኃይሎች ኅብረት መኖሩ ለትግል አስፈላጊ መሆኑ የሚካድ አይደለም:: የኢሕአፓ የ36 ዓመት ተመክሮ ኅብረት ህያው በሆኑና በእርግጥም በትግሉ ሜዳና አውድማ ሚዛን ባለው ህልውና በሚንቀሳቀሱ ድርጅቶች መሀል መሆን እንደሚገባው ያመለክታል:: በድርጅቶች መሀል ሊኖር ከሚችለው ኅብረት ባሻገር ግን ድርጅቱ ከሕዝብ አንፃር ሰፋ ያለውን ሊያስተባብር በሚችል ፖለቲካ መኳዝ የሚመለከት በመሆኑ ኢሕአፓ ባለው አቅም ሁሉ ብዙሀኑን ለማቀፍ ጥሯል:: በዚህም መሠረት በአሁኑ ጊዜ ሀገርን ማዳን የሚለው ተልዕኮ ከሁሉም በላይ ነውና ሁሉንም ሀገር ወዳድ የማስተባበሩ ጉዳይ ተቀዳሚ ሆኖ ይገኛል:: ኅብረቱም ሆነ ሕዝብን የማደራጀቱ ጥረት በዚሁ መሠረት መሆን እንዳለበት ኢሕአፓ ያምናል፣ ለማሳመንም ጥረቱን ይቀጥላል::

ኢሕአፓ ከተመሠረተ ጀምሮ ምን ፈየደ፣ ምን ድል አስመዘገበ ብለው የታሪክን ሂደትና ይዘት ነጭ ጥቁር በሚል ሥልጣን መያዝ ድል አለመያዝ ሽንፈት ብለው የሚደመድሙ ዛሬም መኖራቸው የሚታወቅ ነው:: ባላወቀው ፈራጁ በዝቶ ነው:: የየካቲት አብዮት የእነአበራ ገሙ፥ የነገርማሜ ንዋይ፥ የነከበደ ነቅንቅ፥ የነታከለ ወልደ ሐዋርያት፥...ወዘተ ሁሉ፣ የባሌና ጎጃም አርሶ አደሮች አመፅ፣ የሜጫ ቱለማ እንቅስቃሴ አንደምታ፣ የተማሪዎች ትግል ሁሉ ውጤት ነው:: እያንዳንዱ ትግል በመለሰተኛም ደረጃ ማህተሙና ጫናውን እያሳረፈ ለቀጣዩ መንደርደርያ እየሆነ አስተዋፅዖ አድርጓል:: ዛሬ በፓርቲ መደራጀት ስንል፣ የሴቶችና የውሁዳን መብት ስንል፣ ዴሞክራሲ አለገደብ ስንል፣ ባለነፍጥን ማሸነፍ ይቻላል ስንል፣ በምስጢር መደራጀት ስንል፣ ወዘተ... የኢሕአፓን ድርሻና አስተዋፅዖ መካድ አንችልም:: ዛሬ በሥልጣን ላይ ያለው በፈለገውና ባፈተተው መግዛትና መፈንጨት ሲያቅተው የሚጎረብጥና የነቃ ሕዝብ በቦታው መገኘቱ ያለፈው ትግል ድል ነው:: ትግል እንደ ኳስ ጨዋታ ሦስት ያገባ አሸነፈ ሁለት ያገባ ተሸነፈ በሚል የሚገመገም አይደለም:: የሕዝብ ትግል የደም ግብርን ከፍሎ የታሪክን ጉዞ በፈለገበት አቅጣጫ ይጎትታል:: ወደ መጨረሻ ድሉ ደረሰ አልደረሰ ድልን እያስመዘገበ ይጓዛል:: በመሆኑም ኢሕአፓ በርካታ ድሎችን ተቀዳጅቶ፣ አሸናፊም ነው:: የፖለቲካ ሥልጣን ገና በሕዝብ እጅ ሊገባ ስላልቻለ ብቻ የሕዝብን መራራና ታሪካዊ ትግል ተሸንፏል ብሎ ቀቢፀ ተስፋንና ጨለምተኝነትን ማንገሱ ትክክል አይደለም::

ለረጅም ዘመን የኢትዮጵያ ሕዝብ ዴሞክራሲን ፍለጋ ሲማስንና ሲደማ ቆይቶ ዛሬ ከድል አፋፍ ላይ ገና ባይደርስም ያለፈበትን ሂደትና ዙሪያ ገባውን ለመገምገምና የሚያዋጣውን ስልትና ዘዴን ለመቀየስ ግን በቂ ተመክሮ ገብይቷል:: የ36 ዓመቱ ኢሕአፓ የዚህ መሳሪያና ነፀብራቅ ነው:: ሀገር ከል ለብሳ ስታነባ፣ ግፍና አፈና በሕዝብ ላይ ሲባርቅ፣ አንደበት ሁሉ በአምባገነኖች በታፈነበት፣ ተስፋን ጨለማ ውጦ ቀቢፀ ተስፋ በነገሰበትና የኑሮ ጣጣዎች በራሳቸው ገነው ዜጋን ሲወዘውዙ በነበረበት ጊዜ ኢሕአፓ ተስፋን አስቀድሞ፥ ደፍሮና የጀግኖች አርበኞችን ወኔ ተላብሶ፣ ጨቋኙን ማቸነፍ ይቻላል በሚል የጀመረው ትግል ያረመሙት አንደበት አግኝተው እንዲናገሩና ጭቁኖችም አብዮታቸውን እንዲያካሂዱ አድርጓል:: ይህ የሀገሪቷን ይዞታና አካሄድ ለአንዴም ለሁሌም የለወጠ መሆኑ እንዴትስ ሊካድ ይችላል? ጊዜ ባለፈ ቁጥር ሐቁ ላይ ጭራና ቀንድ እየቀጠሉ የኢሕአፖንም የሕዝብንም ታሪክና ገድል ከንቱ ሊያደርጉ የሚፍጨረጨሩ ከላሾችና በራዦች ቢርመሰመሱም ቅሉ የ36 ዓመት መራራ ትግል በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ሚዛኑ ከፍ ያለ ነው:: ይህ ቢባልም ድርጅቱ ከግብ ለመድረስ ግን ገና ብዙ ውጣ ውረድ እንዳለበት ግልፅ ነው:: ከዚህ ቀደም ብለን እንደነበረውም

> "በጥራዝ ነጠቅነት መክነፍን፣ በሌጣ ትርጓሜ መጋለብን፣ እንዳፈተተ መቆንፀልን ለማስቀረትና በዚህም ምክንያት የሚፈጠረውን የተሳከረ ሂደትና መመሳቀል ፈር፥ አቅጣጫ ለማስያዝ፣ ፖለቲካዊ ትንታኔዎች አየር ላይ መጥቀው በሕዝብ አናት ላይ የሚበሩ ሳይሆኑ ወረድ ብለው ከሕዝቡ ወዝ ጠረን ጋር እየተዛመዱ፣ የህዋሳቱን ንዝረት የሚያሰሙ፣ ስሜቱን በትክክል

የሚተረጉሙ፤ ምኞቱን የሚያንፀባርቁ እንዲሆኑና የኢትዮጵያ ፖለቲካዊ እድገት ድልደላ መሠረት ላይ እንዲዋቀር ከማድረግ አኳያ” የኢሕአፓ ሚና በቀላሉ የሚታይ አይደለም፡፡

ኢሕአፓ ሲመሠረትም ሆነ ህልው ሆኖ ሲታገል የምርጦችና የጥቂቶች ድርጅት አልነበረም-- የሕዝብ እንጂ፡፡ ተማሪውና ምሁሩ፥ ተራማጁና ወጣቱ በድርጅቱ ሚናው ደማቅ የነበረና ያለ ቢሆንም አርሶ አደሩ፥ ላባደሩ፥ ወታደሩ፥ የቤት ሠራተኞች፥ ጫማ ጠራጊው፥ ነጋዴው፥ መንገድ አዳሪው፥ የእኔ ብጤው ሁሉ የኢሕአፓ አባልም ደጋፊም ሆነው ሰፊ ሕዝባዊ መሠረትና ይዘት ሰጥተው እስከዛሬም ጠብቀው አቆይተውታል፡፡ ዛሬም ቢሆን በበሊኅ አዕምሮና ፅናት እየታገለ ያለው ድርጅት ላይ የተነሱበት የሀገር ጠላቶችና ማፈሪያ ቅጥረኞች አሉና ሀገር ወዳጹ ዜጋ አደብ ገዝቶ፤ ወኔውን አጠናክሮ፤ በርቀት ቃኝቶ ወያኔን የሚያደባይ ቆራጥ ትግል ማካሄድ አለበት፡፡ ስህተትን መድገምና ነጋ ጠባ ደግሞ በወያኔና ሀሳዊ መሲሆቹ መሞኘትም ማብቃት ያለበት ነው፡፡ ኢሕአፓ 36 ዓመት በትግሉ መሪር ጎዳና ተጉዟል፡፡ ገና ሌላ 36 ዓመት ቢጠይቅም ኢሕአፓ ሀገርና ሕዝብን ለደከመኙ ሰለባ አድርጎ አሳልፎ አይሰጥም፡፡ ቃል ኪዳኑን ያድሳል እንጂ አያፈርስም፡፡ ለክህደትና ውርደት፥ ለሽንፈትና ተለጣፊነት ባዳና ጠላት እንደሆነም ይቀጥላል፡፡ በሕዝብ አቸናፊነት ላይ ያለው እምነቱ ያኔ ሲመሠረት በነበረው ደረጃ እንደፀና ነው፡፡

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!

እናቸንፋለን!!!